# የእርጅና እና ማህበረሰብ ኑሮ ዲፓርትመንት

## የአረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች (EPD) ወይቨር ፕሮግራም

የ EPD ወይቨር ፕሮግራም የቤት ነርሲንግ የምያስፈልጋቸው የዲሲ ነዋሪዎች ቤቤታቸው ወይም እገዛ ላይ የተመሰረተ ማህበረሰብ ውስጥ እየኖሩ አገልግሎቶችን እና እገዛዎችን እንድያገኙ ይፈቅዳል።

እንደ መመገብ፣ ልብስ መልበስ፣ መጸዳጃ ቤት መጠቀም፣ ሰውት መታጠብ ከመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ጋር በተያያዘ እገዛ የሚሹ ከሆነ፣ የ EPD ፕሮግራም ሊጠቅሞት ይችላል።

**ለ EPD ወይቨር ፕሮግራም ብቁ ለመሆን፣ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርቦታል:**

የአሜሪካ ዜጋ መሆን ወይም ለ Medicaid ብቁ የምያደርግዎ የስደተኝነት ደረጃ ሊኖሮት ይገባል;

የኮሎምብያ ዲስትሪክት ነዋሪ መሆን ይኖርቦታል;

አረጋዊ (ዕድሜዎ 65 አመት እና ከዚያ በላይ የሆነ) ወይም በ 18-64 የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ አካል ጉዳተኛ መሆን ይኖርቦታል;

DC በዲሲ Medicaid አቅራቢ የተሞላ የሐኪም ትእዛዝ ቅጽ (POF) ሊኖሮት ይገባል;

Liberty Healthcare ጋር በመሄድ የፊት-ለ-ፊት ግምገማ ተደርጎሎት "የፍላት ደረጃ" የወጣሎት መሆን ይገባዎታል;

በአንድ ግለሰብ ከ $4,000 የማይበልጡ የሚቆጠሩ ንብረቶች(ለምሳሌ፣ የቁጠባ ወይም ቼክ ሒሳብ) ሊኖሮት ይገባል; እንዲሁም

በ 2022 ሊቆጠር የሚችል ከ $2,523 የማይበልጥ ወርሃዊ ገቢ ያለው ወይም የ Medicaid ብቁነት ትርፍ ክፍያ መጠን ማሟላት የሚችል መሆን አለበት።



## ዛሬውኑ ያናግሩን

የእርጅና እና የማህበረሰብ ኑሮ ዲፓርትመንት
እርጅና እና የአካል ጉዳት ሪሶርስ ማእከል (ADRC)
250 E Street SW
ዋሺንግተን፣ ዲሲ 20024
ኢሜይል:
EPDWaiver.dcoa@dc.gov

(202) 724-5626 | ፋክስ: | (202) 724-2008
8:30 ኤኤም – 4:30 ፒኤም

**በ EPD ወይቨር ፕሮግራም ስር የሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:**

የኬዝ አመራር – የ EPD ወይቨር ፕሮግራም ስር የሚገኙ አገልግሎቶችን ለመለየት እና ለማስተባበር ማህበራዊ ሰራተኛ ከእርስዎ ጋር ይሰራል;
የግል እንክብካቤ እርዳታ (PCA) አገልግሎቶች – የሰለጠነ ሙያዊ እርዳታ ሰጪ ወደ ቤትዎ ይመጣ እና እንደ እርስዎን ማስዋብ፣ ልብሶችዎን ማልበስ፣ ምግብ መመገብ፣ መጸዳጃ መጠቀም፣ ወዘተ በመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ይረዳዎታል;
የግል ኢመርጀንሲ ምላሽ አገልግሎቶች (PERS) – ሰዎች ደውለው እገዛ እንዲጠይቁ የሚፈቅድ ኤሌክትሮኒካዊ አገልግሎት;
አገልግሎቶች My Way – አገልግሎቶች እንዴት ሊቀርቡልዎ እንደሚገባ እና ማን ልያቀርብልዎ እንደሚገባ የሚወስኑበት ፕሮግራም; እንዲሁም
እገዛ ላይ የተመሰረተ ኑሮ - ፍቃድ ያላቸው የቤት ተሳታፊዎች ነጻነታቸው ለመጠበቅ ሲባል ቤት ውስጥ እየኖሩ የሚፈልጉዋቸው አገልግሎቶች ማግኘት ይችላሉ።

DACL DEPARTMENT OF AGING AND COMMUNITY LIVING | DHCF The Department of Health Care Finance INVESTING IN YOUR HEALTH | WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR